# የስብሰባ ጥሪ

## ለአጋር ማይክሮ ፋይናንስ አክስዮን ማህበር ባለአክስዮኖች በሙሉ

- የማህበሩ የተከፈለ ካፒታል፡ 370,372,200.00
- የማህበሩ ምዝገባ ቁጥር፡ LD/AA/3/0003015/2008
- የማህበሩ አድራሻ፡ አ/አ ከተማ፣ ልደታ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ፡ 08፣ ዳማ ህንጻ 3ኛ እና 5ኛ ፎቅ

የአጋር ማይክሮ ፋይናንስ አክስዮን ማህበር የባለአክስዮኖች 20ኛ መደበኛ እና 13ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በኢትዮጵያ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 366፣ 367፣ 370፣ 371፣ 372 እና 393 መሰረት ሚያዚያ 12 ቀን 2016 ዓ.ም ከጧቱ 2፡00 ጀምሮ በራስ ሆቴል የስብሰባ አዳራሽ ይካሄዳል፡፡ በመሆኑም የማህበሩ ባለአክስዮኖች በአካል ወይም በህጋዊ ወኪሎቻችሁ አማካኝነት በተጠቀሰው ሰዓት፣ ቀን እና ቦታ እንድትገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን እያስተላለፈ በንግድ ህጉ አንቀጽ 380 መሰረት የጉባኤው ድምጽ ቆጣሪዎች ተሰይመው እና ምልዓተ ጉባኤው መሟላቱ ተረጋግጦ ጉባኤዎቹ የሚጀምሩ መሆኑን ይገልጻል፡፡

### የ20ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

1. የጉባኤውን አጀንዳዎች ማጽደቅ፣
2. ከ19ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በኋላ የተደረጉ የማህበሩን አክስዮን ዝውውሮች እና አዳዲስ አክስዮን የገዙ ባለአክስዮኖችን ተቀብሎ ማጽደቅ፣
3. የጉባኤውን ቃለ-ጉባኤ ማጽደቅ፣

### የ13ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

1. የጉባኤውን አጀንዳዎች ማጽደቅ፣
2. የማህበሩን መመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪ ደንብ ማሻሻል፣
3. የማህበሩን ካፒታል ለማሳደግ በ10ኛ እና 12ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነውን የካፒታል ማሳደጊያ ጊዜ በሚሻሻልበት ሁኔታ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፣
4. እ.ኤ.አ በ2022/23 ሂሳብ ዓመት ባለአክስዮኖች ባገኙት የትርፍ ድርሻ ለተደለደለላቸው አክስዮን ክፍያ በመፈጸም እንዲሁም በነባር እና አዲስ ባአክስዮኖች በጥሬ ገንዘብ ተገዝቶ ያደገውን የማህበሩን ካፒታል ማጽደቅ፣
5. የጉባኤውን ቃለ-ጉባኤማጽደቅ፣

*<u>ማሳሰቢያ</u>*

- ባለአክስዮኖች ለስብሰባ በሚመጡበት ጊዜ ማንነት የሚገልጽ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- በጉባኤው ላይ በአካል መገኘት የማይችል ባለአክስዮን በንግድ ህጉአንቀጽ 373 መሰረት በወኪሎቻቸው አማካኝነት መሳተፍ የምትችሉ ሲሆን፣ ጉባኤው ከመካሄዱ ከሶስት ቀናት በፊት ልደታ ባልቻ ሆስታል ጀርባ ዳማ ህውስ ህንጻ ላይ ሶስተኛ ፎቅ በሚገኘው የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት የፋይናንስ እና ኢንቨስመንት መምሪያ ቢሮ ቁጥር 306 ቀርበው ለዚሁ ጉዳይ የተዘጋጀውን የውክልና ስልጣን መስጫ ቅጽ በመፈረም ወይም በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ አገልግሎት በኩል ወይም ሌላ አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ የውክልና ስልጣን ለወኪሎቻችሁ መስጠት አለባችሁ፡፡
- የባለአክስዮኖች ህጋዊ ወኪሎች የወካያቸውን የቀበሌ መታወቂያ ወይም መንጃ ፍቃድ ወይም ፓስፖርት ቅጅዉን እንዲሁም በጉባኤው ለመሳተፍ እና ድምጽ ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ስልጣን ማስረጃ ዋናውን እና ቅጅውን እንዲሁም ማንነትን የሚገልጽ የራሳቸውን የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም መንጃ ፍቃድ ወይም ፓስፖርት ዋናውን እና ቅጅውን ይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

*የአጋር ማይክሮ ፋይናንስ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ*